የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY
☎+251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251- 55 12 56 Fax +251- 55 31 55
Po.Box 17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa Ethiopia. Website:- www.aeup.org E-mail lionco.ethionet.et

ቁጥር
Ref.№______________
ቀን
Date ______________

### ከመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት/ መኢአድ/

# የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ፣

# ለፓርቲ ውሳኔ እና ደንብ የማይገዛ አመራር ሆነ አባል ይዞ መጓዝ ለድርጅቱ ጠንቅ ነው!

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት/መኢአድ/ የተመሠረተው የዜጐችን ሰብአዊ፣ ዲሞክራሲያዊ እና የህግ የበላይነት ለማስከበር፣ ዲሞክራሲያዊ ስርአት በሀገራችን ስፍኖ ዜጐች በእኩልነትና በነፃነት የመኖርና የመስራት ህገመንግስታዊ መብታቸው ዋስትና እንዲረጋገጥ ታስቦ መሆኑ ሁላችንም የምናውቀው እውነታ ነው፡፡ ፓርቲያችንም ከገዥው ፓርቲ የሚለይበት አንዱ መገለጫ በዚሁ ጠንካራ መርሁ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በፓርቲው ውስጥ ያሉ ጥቂት አባላትና አመራሮች የፓርቲያችንን ህግና ደንብ በመጣስ የአምባገነንነት ባህሪ ከማንፀባረቃቸውም ባሻገር ፓርቲውን እነሱ እንደፈለጉ ካልመራን በማለት፣ ታህሳስ 17 ቀን 2003 ዓ.ም መሰሎቻቸውን አሰባስበው በእብሪት በመንቀሳቀስ፣ የፓርቲያችንን የውጭ ትግል ትተን ወደ ውስጥ ትግል በማተኮር ወርቃማ ጊዜያችንን እንድናባክን ከማድረጋቸውም ሌላ በአባላትና በህዝብ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ለመፍጠር ሞክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህም ሆኑ በተለያዩ ጊዜያት የተፈጠሩት ተመሳሳይ ሥርአት-አልበኛ ግለሰቦች አንዳቸውም ከፓርቲው እየተንጠባጠቡ ከመቅረት የዘለለ ውጤት አላመጡም፡፡

መኢአድ እስከአሁን ከገጠሙት ችግሮች ባልተናናሰ እና እንዲያውም በባሰ መልኩ ተፈታትነውት የነበሩት ጥቂት የሥልጣን እና የጥቅማጥቅም ጓደኞች በሁለተኛው መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤአችን ዋዜማና ማግስት ያደረጉት እንቅስቃሴና ፓርቲውን ለማፍረስ ያደረጉት ዘመቻ በቀላሉ የሚታይ ክስተት አልነበረም፡፡

መኢአድ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምዕራብ እስከ ምስራቅ፣ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች በሚኖሩ ዜጐች የገጠሩንም ሆነ የከተማውን ህዝብ መሠረት አድርጐ የተዋቀረ ጠንካራ ህዝባዊ ፓርቲ በመሆኑ፣ በፓርቲው ውስጥ የተሰባሰቡ፣ በጥቅም የተሳሰሩ ጥቂት የአንድ ጉጥ ልጆች፣ ከጥበቃ ሠራተኞች ጀምሮ ሌሎች ሠራተኞች በማስተባበር፣ አንዱን እየነቀሉ ሌላውን እየተከሉ፣ እንደፈለጋቸው ሲፈነጩ የኖሩት አንሶ፣ አሁን

ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ ተስፋ የሆነውን ፓርቲ የዕለት ከዕለት ሥራ በማደናቀፍ አሉታዊ ተፅዕኖ ለመፍጠር በመሞከር ላይ ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ በመኢአድ የቁርጥ ቀን ልጆች የተባበረ ኃይል ከአሁን በፊት አንጃ ለመፍጠር የተንቀሳቀሱ ኃይሎች ጥረት እንደመከነ ሁሉ፣ አሁንም የሰሞኑ የጉጠኞች እንቅስቃሴ እንዲከሽፍ ተደርጓል፣ ለወደፊትም እንዲከሽፍ ይደረጋል፡፡

መኢአድ ከታህሣሥ 15 እስከ 17 2003 ዓ.ም ሁለተኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ለማካሄድ በዝግጅት ላይ አንዳለ የውጭና የውስጥ ኃይሎች በፓርቲያችን ህልውና ላይ አደጋ ለማስከተል በማሰብ በተለያዩ ድረገጾች መኢአድ ሊበተን ነው፣ ሊፈርስ ነው፣ ከማለት ጀምረው ጠቅላላ ጉባኤውን ለመበጥበጥ እና ለማወክ፣ በአመራር አካላትና የፓርቲ አባልነት የተሰለፉ የውስጥ ኃይሎች ለውጭ ኃይሎች መሣሪያ ሆነው ሲንቀሳቀሱ መታየታቸውን ያረጋገጥነው ሃቅ ነው፡፡ መኢአድ በዚህ ጠቅላላ ጉባኤ ወቅት ሲፈታተኑት የነበሩትን ኃይሎች እንቅስቃሴያቸውንና ማንነታቸውን በሁለት ከፍሎ ያያቸዋል፡፡ ይሄውም፡-

1. በፓርቲው ውስጥ የነበሩ ጥቂት አመራሮችና አባላት፣ በሌላ አገላለጽ የስልጣን እና የጥቅማ ጥቅም አሳዳጆች ሲሆኑ፣
2. ሌሎች ደግሞ ከአሁን በፊት በፓርቲው ውስጥ በሰሩት ጥፋት በድስፒሊን የታገዱ እና ራሳቸውን "የመኢአድ የመፍትሄ አፈላላጊ ቡድን" ብለው የሰየሙት ናቸው፡፡

## 1. <u>የሥልጣንና የጥቅማጥቅም አሳዳጆች</u>

መኢአድ የሁለተኛውን ጠቅላል ጉባኤ ለማድረግ በሚዘጋጅበት ወቅት ጥቂት የስልጣን እና የጥቅማ ጥቅም አሳዳጆች የአንድ የጉጥ ልጆች የፓርቲው ፕሬዝደንት ከስልጣን እንደሚለቁ በመግለጻቸው ራሳቸውን የፓርቲ ፕሬዝደንትና ተቃዳሚ ም/ፕሬዝደንት እንዲሁም ዋና ፀሀፊ ለማድረግ ከፓርቲያችን ደንብና ህግ ውጭ ተንቀሳቅሰዋል፡፡

በቅድመ-ጉባኤ ዝግጅታችን ወቅት የዝግጅት ኮሚቴነቱን ቦታ በመያዝ፣ (i) የጠቅላላ ጉባኤ አባላትን ቁጥር በማብዛት፣ (ii) ጉባኤው ላይ ሊካፈሉ የሚገባቸውን አባላት በማስቀረት እና በምትካቸው እነርሱን የሚደግፉ ግለሰቦችን በማሰባሰብ እንዲሁም (iii) በሌሎች የጉባኤ አባላት ላይ የራሳቸውን ፍላጐት በሀይል ለመጫን ያደረጉት ሙከራ ቀላል የማይባል ፈተና ነበር፡፡ በጉባኤውም ወቅት ከጉባኤ አባላት ውጭ የሆኑ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ግለሰቦች አሰርገው በማስገባት ጠቅላላ ጉባኤው በውጥረት እንዲጠናቀቅ ከማድረጋቸውም ባሻገር ጠንካራ የፓርቲ አመራሮች እንዳይመረጡ ያደረጉት ከፍተኛ ዘመቻ ቀላል የማይባል ውጥረት ፈጥሮ ነበር፡፡

በተጨማሪም የፓርቲውን አመራር በዘር እና በጐሳ በመከፋፈል እገሌ ኦሮሞ ነው፣ እከሌ ትግሬ ነው፣ ወዘተ በማለት ፓርቲያችን የማያምንበትን እና የማይቀበለውን የጐሣ አደረጃጀት ከጉባኤው በፊት ለመቀስቀሻነት መጠቀማቸው በእጅጉ የሚያሣዝን እና የሚያሣፍር ተግባር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

እነዚህ የስልጣንና የጥቅማጥቅም አሳዳጆች በወንዜኝነት ገመድ ተሳስረው በጠቅላላ ጉባኤው ወቅት ይቀርብ የነበረውን የኦዲት ሪፖርት እንዳይጠናቀቅ በማድረጉ ሂደት ከባድ ሚና ተጫውተዋል፡፡ በመኢአድ የጉባኤ ታሪክ ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ መልክ ለጉባኤው እንዲቀርብ ያደረጉት የገቢና የውጪ ሂሳብ የማይጣጣም መሆኑ፣ በኦዲተር እስከሚረጋገጥ ድረስ መጠበቅ የሚገባ ቢሆንም፣ በፓርቲያችን የሂሳብ አያያዝ ችግር መኖሩን ጠቋሚ ነው፡፡

የመኢአድ ጠቅላላ ጉባኤ ይህንን ከደንብ ውጭ የሆነ እንቅስቃሴ በመታዘብ ኘሬዚደንቱ፣ ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል፣ በኘሬዝደንትነት እንዲቀጥሉ በማድረግ በፓርቲው ውስጥ ሥር የሰደደውን የቡድንተኝነት ገመድ እንዲበጣጥሱና የፓርቲውን አመራር እንዲያጠሩ ሙሉ ስልጣን ሰጥቷቸዋል፡፡ በጉባኤውም በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት በሙሉ ድምጽ የተመረጡት ኘሬዝደንት ተቀዳሚ ም/ኘሬዝደንት እና ሌሎች 17 የስራ አስፈጻሚ አባላት ዝርዝር ለጠቅላላ ጉባኤ አባላት አቅርበው እነሱም በሙሉ ድምጽ ተመርጠዋል፡፡ በተጨማሪም እንደአስፈላጊነቱ የስራ አስፈፃሚ አባላትን መለወጥ እንዲችሉ እና ከአሁን በፊት የቀጣና ም/ኘሬዝደንቶች ይባሉ የነበሩት ተሰርዞ ከአሁን በኋላ የቀጣና አስተባባሪዎች በሚል እንዲሰየሙ ጠይቀው እነዚህም በጠቅላላ ጉባኤ ሙሉ ድምጽ ጸድቀዋል፡፡

አሁን በአጀኝነት የሚንቀሳቀሱ ሀይሎች በወቅቱ በተደረገው የተቀዳሚ ም/ኘሬዝደንት፣ የሥራ አስፈፃሚ ምርጫ እና ሌሎች ውሣኔውች ላይ አንዳችም ተቃውሞ አለማሰማታቸው ምርጫዉ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የተከናወነ በመሆኑና ለሚያነሱት ተቃውሞ የጉባኤዊ አባላት እንደማይቀበሏቸው በመረዳታቸው ነበር፡፡

ይሁን እንጂ በጥቅምና በመንደርተኝነት የተሳሰረው አንጃ የቋመጠለትን የፓርቲ ስልጣን በማጣቱ “ማሽላ ሲያር ይስቃል” በሚለው ብሒል ተሸፍነው ጉባኤውን ቢጨርሱም ከጉባኤው ማግስት እና ሣልስት ጀምሮ ከጉባኤው በፊት ያደርጉት የነበረውን የቡድንተኝነት እንቅስቃሴ በመቀጠል የጠቅላላ ጉባኤውን ውሣኔ አንቀበልም፣ በማለት ወደእየ አካባቢያቸው ለተመለሱ የጉባኤ አባላት ስልክ በመደወል ማወክ ቀጠሉ፡፡ ይህም ሂደት አግባብ ባለመሆኑና በተለይም በጉባኤው ማግስትና ሣልስት ያደርጓቸውን የስነ ስርአት ጥፋቶች አስመልክቶ በሦስት የስራ አስፈጻሚ አባላት ላይ ማስጠንቀቂያ በመስጠቱ የበለጠ የቡድኑን ሥርአተ-አልባኝነት ይፋ ያወጣበት ሂደት ነበር፡፡

የፓርቲው ኘሬዝደንት በድህረ-ጠቅላላ ጉባኤ የመጀመሪያውን የስራ አስፈፅሚ ስብሰባ ታህሣስ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ጠርተው አጀንዳውን ከአፀደቁ በኋላ አንደኛው የአጀንዳው ርዕስ “ራስን መውቀስ እና እርስ በርስ መወቃቀስ” ውይይት በሚደረግበት ወቅት የጥቅማ ጥቅም አሳዳጆች እና የአንድ ጐጥ ልጆች መሪ የሆነው የፓርቲን ዲስኘሊን ያልጠበቀ የኘሬዝደንቱን እና የስራ አስፈፃሚውን ክብር የጣሰ ንግግር እና ዘለፋ በመሰንዘሩ፣ ችግሩን የሚያጣራ ገለልተኛ አጣሪ ኮሚቴ ተቋቋመ፡፡ አጣሪ ኮሚቴው ስራውን እየሰራ ባለበት ወቅት እነዚህ ጐጠኞች፤ (i) ከመኢአድ ህገ ደንብ ውጪ የጥበቃ ኃላፊው የጽህፈት ቤት ቁልፍ ይዞ እንዲሰወር እና ቢሮዎችን በመዝጋት ስራ አስፈጻሚው እንዳይጠቀምባቸው በማድረግ፣ (ii) ሁለት ነባር የጥበቃ ሠራተኞች አባርረው በምትካቸው የእነሱ አካባቢ ተወልጆች በመቅጠር፣ (iii) የንብረት ክፍል ሰራተኛውን፣ (iv) የመዝገብ ቤት ሰራተኛውን እና (v) አንድ አደራጅ በድምሩ አምስት የፓርቲውን ሠራተኞች በማስተባበር የፓርቲውን ማህተም፣ አርማ ያለው የመፃፃፊያ ወረቀት እና ሌሎችም ቁሳቁሶች እንዳንጠቀምበት መከልከል ያንጃ ቡድኑ ዋና ዋና የጥፋት እንቅስቃሴዎች ነበሩ፡፡ በተጨማሪም ጥር 2/2003 ዓ.ም የሰንደቅ ጋዜጣ ጋዜጠኛ ጠርተው የፓርቲውን ኘሬዝደንት ኢንጀነር ኃይሉ ሻውልን ወያኔ ናቸው፣ አውርደናቸዋል፣ በማለት በሦስቱ ስራ አስፈጻሚ አባላት ዙሪያ የሚንቀሳቀሱት ጥቂት ግለሰቦች የሰጡት መግለጫ የአንጃውን ዝቅጠት ያመላከተ ነበር፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በጠቅላላ ጉባኤው ወቅት ከስራ አስፈፃሚ የተሰናበቱት አቶ ገ/ጻዲቅ ኃ/ማርያም፣ ም/ኘሬዝደንት ነኝ፣ ማንም አያወርደኝም፣ በማለት በ14/05/2003 ዓ.ም ለአዲስ አድማስ ጋዜጣ የሰጡት መግለጫ የዚሁ የቡድንተኝነት ሂደት ማረጋገጫና የጠቅላላ ጉባኤውን ውሳኔ አለመቀበላቸውን ያስመሰከሩበት ተጨማሪ ሂደት ነበር፡፡

ከዚህም ሌላ በፓርቲው ኘሬዝደንትና በሌሎችም የሥራ አስፈፃሚ አባላት ላይ የሚሰነዘሩ ስም ማጥፋትና ዛቻዎች እንዲሁም "እንገድላችኋለን" የሚሉ የስልክ ማስፈራራት የአንጃው ቡድን ማንነትን ያረጋገጠ ተግባር ነው፡፡

መኢአድ እንደእነዚህ አይነት ሥርአተ-አልበኛ እና አምባገነን የሆኑ ጥቂት የአመራር አባላት ሲያጋጥሙት ዝም ብሎ ማየት የፓርቲውን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል በመሆኑ ሦስት የስራ አስፈፃሚ አባላትን፣ ስድስት የላዕላይ ም/ቤት አባላትንና አምስት የፓርቲ አባላት፣ በድምሩ አስራ አራት ሰዎች እንዲታገዱ እና ጉዳያቸው በዲስኘሊን ኮሚቴ እንዲታይ አድርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ጉዳያቸውን በደንብና በስርአት ተካታትለው ውሳኔውን ከመጠበቅ ይልቅ በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ ያልተሰጣቸውን ስልጣን በመጠቀም በጠቅላላ ጉባኤ ያጣውን ኃላፊነት እና ሥልጣን ሌላው የጥቅማ ጥቅም ቡድን መሪ እራሱን ም/ኘሬዝደንት ብሎ በመሰየም በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡትን የፓርቲያችንን ኘሬዝደንት፣ ተቀዳሚ ም/ኘሬዝደንት፣ ዋና ፀሀፊና የድርጅት ጉዳይ ሀላፊ ማገድን አስመልክቶ ቡድኑ መግለጫ ከመስጠት በተጨማሪ የፓርቲው አመራርና አባላት መኢአድ ጽ/ቤት እንዳይገቡ በመከልከል እና ፓርቲውን የግል ድርጅታቸው በማስመሰል ከስልጣናቸው በላይ ተንቀሳቅሰዋል፡፡ ይሄንንም ድርጊታቸውን በመቃወም የዞን አባላትና አመራር እንደሁም የአዲስ አበባ አመራርና አባላት እነዚህን ሥርአት አልበኛ አንጃዎች ከጽ/ቤቱ ማስወጣት አለብን በማለት ለመንቀሳቀስ ቢጠይቁም የፖርቲያችንን ክብርና የህዝባችንን ሥነ ልቦና ለመጠበቅ ሲባል ጉዳዩን ለፍ/ቤት አቅርበን እንዲወሰን አድርገናል፡፡ በዚህም መሠረት በፈፀሙት ወንጀል እንዲጠየቁና ቢሮአችንንም ለቅቀው እንዲወጡ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት መደበኛ የፓርቲውን ስራ እነሆ ከሰሞኑ ጀምረን በመንቀሳቀስ ላይ እንገኛለን፡፡

በሌላ በኩል ግን እነዚህ የጥቅማ ጥቅም አሳዳጆች የፍ/ቤት ትእዛዛ እግዱን ሊሰጡ በመጡ ኃይሎችና እንዲታሸጉልን በጠየቅናቸው ቢሮዎች ላይ የእሽጋው ስርአት ሲከናወን የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ በመጣስ ለመቃወም ሲሞክሩ መታየታቸው ምንኛ ለህግና ለደንብ የማይገዙ መሆናቸውን ያጋለጠ እና ስለዲሞክራሲ የሚናገሩበት ሞራል ጨርሶ የሌላቸው መሆኑን ያረጋገጠ ተግባር ነው፡፡

በአጠቃላይ የመኢአድ አወቃቀር በአስተዳደር ዞኖች የተመሠረተ በመሆኑ ፓርቲውን አዲስ አበባ ውስጥ በሚንቀሳቀሱ ማናቸውም ሃይሎች በቀላሉ የማይናወጥ መሆኑን ያልተገነዘቡ ጥቂት ጥቅም አሳዳጆች ሊያፈርሱ ሙከራ አድርገዋል፡፡ የሚገርመው ግን ከእነዚህ ግለሰቦች መካከል ጥቂቱ ይህን እውነታ የሚያውቁ ቢሆንም አፍራሽ ሃይሎች አደራጅተው ዞኖችን ለማሳሳት ሞክረዋል፡፡ ይሁን እንጁ አንዱንም የዞንም ሆነ የወረዳ ስራ አስፈፃሚዎች ድጋፍ ሊያገኙ አልቻሉም፡፡ በተቃራኒው ዞኖች እና ወረዳዎች በመደበኛ ሁለተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ለመረጡት የአመራር አባላት እና ለተደረጉት ውሣኔዎች ተገዥ በመሆን፣ ከነዚህ ውጪ ማናቸውንም እንቅስቃሴ የማይቀበሉ እና የሚያወግዙ መሆኑን በላኩት ፋክሶች አማካኝነት አረጋግጠዋል፡፡

## 2. የመፍትሄ አፈላላጊ ቡድን ተብዬዎች

ራሳቸውን የመኢአድ የመፍትሄ አፈላላጊ ቡድን ብለው የሚጠሩ ግለሰቦች ይህን አጋጣሚ ተጠቅመው በተለያዩ ኢንተርኔቶች የሚለቅቋቸው አፍራሽ ኘሮፖጋንዳዎች በአባላትና በደጋፊዎቻችን ላይ ተጽእኖ ለማሳደር ቢሞክሩም ውጤታማ አልሆኑም፡፡ ሂደታቸውም አጋጣሚን ጠብቀው የፖርቲያችንን ክብርና ዝና ለማጉደፍ ከመሞከር ያለፈ፣ ለፓርቲው ተቆርቋሪነት ሆኖ አልተገኘም፡፡ ይህ ቡድን ወደ ፓርቲው መመለስ ከፈለገ ላጠፋው ጥፋት እና ከዚያም በኋላ ለወሰደው እርምጃ ይቅርታ በመጠየቅ ወደ

ፓርቲው የመመለስ ህጋዊ ጥያቄ ማቅረብና ውሳኔውን መጠበቅ ሲገባው “የገበያ ግርግርን” ተጠቅሞ ወዴት መምጣት እንደፈለገ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ አይነቱ ሂደት ለፓርቲው ህልውናም ሆነ ለዲሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ዋጋ የሌለው ስለሆነ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት/መኢአድ/ በአፍራሽ ኃይሎች እንቅስቃሴ ሳይደናገጥ የተመሰረተበትን አላማና ብዙ መስዋዕት የተከፈለበትን ትግል ከዳር ለማድረስ ከመቼውም የበለጠ በጽናት ይታገላል፡፡

መኢአድ በትግላችን ህልውናው ይጠበቃል!
ኢትዮጵያ በትግላችን ለዘላለም ትኖራለች!
የካቲት15/ 2003 ዓ.ም
አዲስ አበባ